DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of the Chancellor



ሚያዚያ (April) 22, 2013

ውድ የዲሲፒኤስ ተማሪዎች ወላጆች እና ቤተሰቦች፣

የ 2012-2013 የትምህርት ዓመት በጥቂት አጭር ወራት ጊዜ ውስጥ መገባደዱን ማመን ያዳግታል። እንደሚያውቁት፣ በዚህ ዓመት በጥቅምት (October) እና በመጋቢት (March) ወራት ተፈጥሮ በነበረው አስቸጋሪ አየር ንብረት መዛባት የተነሣ ሦስት የትምህርት ቀናት ትምህርት ቤቶች ዘግተን እንደነበር ይታወሳል። በዚህም የተነሣ በዓመቱ ለተማሪዎቻችን ትምህርት ማዋል የሚጠበቀውን 180 የትምህርት ቀናት ማካካስ ይኖርብናል።

**ቀድሞ ሰኔ (June) 20 ለግማሽ የትምህርት ቀን ተይዞ የነበረውን ሙሉ ቀን እንዲሆን በማራዘም እና የሰኔ (June) 21 ዓርብ ዕለት ግምሽ ቀንን በመጨመር እና አዲሱን የመጨረሻውን የትምህርት ቀን ከትምህርት ቤት መለቀቂያ ሰዓትም በ 12:15 ፒኤም ላይ ከቀትር በኋላ እንዲሆን እናደርጋለን። በተጨማሪም ለወላጅ መምህር ስብሰባ መካሄጃ የተያዘው ሰኔ (June) 3 ቀን፣ መደበኛ የትምህርት ቀን እንዲውል እናደርጋለን።** ቀድሞውኑ የትምህርት ቤት የትምህርት ቀናት መቁጠሪያ ተሰራጭቶ በነበረበት ወቅት፣ **ሰኔ (June) 21** የትምህርት ማሚያ ቀን (make-up day) እንዲሆን ተብሎ ተይዞ ነበር።

ከዚህ በፊት ቀደም ብሎ በወላጅ መምህር ስብሰባ ቀን እንዲካሄዱ ጊዜ ተይዞላቸው የነበሩ ክንዋኔዎች ሁሉ በሌሎች መንገዶች የሚካሄዱ መሆናቸውን ዕውን ለማድረግ፣ ዲሲፒኤስ ከትምህርት ቤቶች ጋር አብሮ አንድ ላይ ይሠራል። እስከ አሁን ድረስ ባለው ጊዜ ስለ ልጅዎ የትምህርት እድገት እርምጃን በሚመለከት ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎን ቀጥታ የልጅዎን መምህር እና/ወይንም የትምህርት ቤት ኃላፊውን ያነጋግሩ፤ ወይም ለ DCPS Critical Response Team ማለትም ቡድን በ (202) 478-5738 ይደውሉ።

ከልባዊ ሠላምታ ጋር፣



Kaya Henderson
ቻንስለር